# I. የበይነመረብ መዘጋት በ2022፡ የዓለም አቀፍ አጠቃላይ እይታ

## የ2022 አጠቃላይ ዴታ እይታ

### በዓመት የተመዘገበ የበይነመረብ መዘጋቶች*




*እነዚህ ቁጥሮች ይህ ሪፖርት እንደታተመ ያለውን የቅርብ ጊዜ መረጃ የሚያንፀባርቁ እና ከዚህ ቀደም ለታተሙት ላለፉት ዓመታት አጠቃላይ ማሻሻያዎችን ያካተተ ነው።

### በይነመረብ የተዘጋባቸው አገሮች ብዛት

| 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | 19 | 26 | 33 | 29 | 34 | 35 |



**ህንድ፡** 84
**ዩክሬን፡** 22**
**ኢራን፡** 18
**ምያንማር፡** 7
**ባንግላዲሽ፡** 6
**ዮርዳኖስ፡** 4
**ሊቢያ፡** 4
**ሱዳን፡** 4
**ቱርክሜኒስታን፡** 4

**አፍጋኒስታን፡** 2 **ቡርኪናፋሶ፡** 2 **ኩባ፡** 2
**ካዛኪስታን፡**2 **ሩሲያ፡** 2 **ሴራሊዮን፡** 2 **ታጂኪስታን፡** 2
**ኡዝቤኪስታን፡** 2

**አልጄሪያ፡**1 **አርሜኒያ፡** 1 **አዘርባጃን፡**1 **ብራዚል፡** 1
**ቻይና፡** 1 **ኢትዮጵያ፡** 1 **ኢራቅ፡** 1 **ናይጄሪያ፡** 1
**ኦማን፡** 1 **ፓኪስታን፡** 1 **ሶማሌላንድ፡**1
**ስሪላንካ፡** 1 **ሶርያ፡** 1 **ቱኒዚያ፡** 1 **ቱርክ፡** 1 **ኡጋንዳ፡** 1
**የመን፡** 1** **ዚምባብዌ፡** 1

**በዩክሬን እና በየመን በግጭት ወቅት የበይነመረብ መዘጋት በውጭ ሃይሎች ተጥሏል።

# በ2022 የበይነመረብ መዘጋትን ያስከተሉ ሁነቶች

**ተቃውሞዎች** በተቃውሞዎች ጊዜ፤ በ16 አገሮች 62 ጊዜ በይነመረብ ተዘግቷል።

**በሂደት ላይ ያለ ግጭት** በመካሄድ ላይ ባሉ ግጭቶች ወቅት 33 ጊዜ የበይነመረብ መዘጋቶች ተከስተዋል

**ፈተናዎች** "የፈተና ማጭበርበርን ለመከላከል" በሚል በ 6 አገሮች ውስጥ በይነመረብ 8 ጊዜ ተዘግቷል

**ምርጫዎች** በ5 አገሮች ከምርጫ ጋር ተያይዞ 5ጊዜ ተዘግቷል።

# በ2022 የበይነመረብ እገዳ ማሳያዎች

## 1. ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች*** እና በይነመረብን እገዳ የተሸፈነው ብጥብጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው።

→ በ14 ሀገራት ውስጥ 48 የበይነመረብ መዘጋቶች ከተመዘገቡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ጋር ይገጣጠማሉ፡-

→ ባንግላዲሽ፣ ኢትዮጵያ፣ ኢራን፣ ዮርዳኖስ፣ ካዛኪስታን፣ ምያንማር፣ ሩሲያ፣ ሴራሊዮን፣ ሶማሊላንድ፣ ሱዳን፣ ታጂኪስታን፣ ኡዝቤኪስታን እና በሂደት ላይ ያሉ የግጭት ቀጠናዎች በዩክሬን

*** የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ግድያ፣ ማሰቃየት፣ አስገድዶ መድፈር ወይም በመንግስት፣ በወታደሮች እና በፖሊስ ወይም በጸጥታ ሃይሎች የሚፈጸሙ የጦር ወንጀሎችን ጨምሮ የጥሰት ማስረጃዎች ያሉባቸውን ጉዳዮች ያጠቃልላል።

## 2. የአገሮች ስር የሰደደ ተደጋጋሚ ጥቃትና ረዘም ላለ ጊዜ የተደረገ የበይነመረብ እገዳ

→ **787+ ቀናት**

በ2022 መገባደጃ ላይ በኢትዮጵያ ትግራይ ክልል የሚኖሩ ህዝቦች ከ2+ ዓመታትበላይ በመገናኛ ዘዴዎች መቋረጥ ውስጥ ኖረዋል፤ ብዙዎች ግንኙነታቸው እስካሁን ተቋርጧል።

→ ከ35ቱ ሀገራት 33ቱ ከ2016 ጀምሮ በተደጋጋሚ በይነመረብን በመዝጋት ይታወቃሉ።

→ **500+ ቀናት**

እስከ መጋቢት 2022 ድረስ በማይናማር ውስጥ ባሉ ብዙ ክልሎች ያሉ ህዝቦች ለ500+ ቀናት በጨለማ ውስጥ ነበሩ።

→ ከ2020 እስከ 2021 ከተከሰተው 8 የበይነመረብ እገዳ ጋር ሲነፃፀር፤ ከ 2021 ጀምሮ በዓለም ዙሪያ 16 የበይነመረብ እገዳ እስከ 2022 ዘልቋል፤ አሁን ላይ 16 የበይነመረብ እገዳዎች ከ2022 ጀምረው እስከ 2023 ድረስ ዘልቀዋል።

## 3. የታለሙ የበይነመረብ እገዳዎችና ሊለካ የማይቻለው ጉዳት

→ በ23 አገሮች ውስጥ 28 በአገልግሎት ላይ የተመሰረቱ የበይነመረብ እገዳዎች በ 2022 ተከስቷል:

አፍጋኒስታን፣ አልጄሪያ ፣ አርሜኒያ፣ አዘርባጃን ፣ ባንግላዲሽ፣ ብራዚል፣ ቡርኪናፋሶ፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ኢራን፣ ዮርዳኖስ፣ ካዛኪስታን፣ ናይጄሪያ፣ ኦማን፣ ሩሲያ፣ ሲሪላንካ፣ ቱኒዚያ፣ ቱርክሜኒስታን፣ ዩጋንዳ፣ ዩክሬን (በሩሲያ ጦር የተጫኑ)፣ ኡዝቤኪስታን እና ዚምባብዌ

→ ድርብርብ ስልታዊ የበይነመረብ እገዳ + ሳንሱር + ክትትል፤

**ኢራን፡** በአገር አቀፍ ደረጃ የበይነመረብ መድረኮችን ታግዳለች + በክልል ደረጃየመገናኛ ቦታዎች ላይ የሰዓት እላፊ አይነት እገዳ በተንቀሳቃሽ መገናኛዎች ላይትጥላለች።

**ምያንማር፡** የተንቀሳቃሽ መገናኛ መረረያዎች ኔትወርኮችን፤< የቪፒኤን አገልግሎትንና ሚስጥራዊ የመልእክት መለዋወጫ መድረኮችን ታቋርጣለች። ሰዎች በወታደር በሚተዳደሩ የግንኙነት አገልግሎት ሰጪ ኔትወርኮችን እንዲጠቀሙ ታስገድዳለች።

**ዩክሬን፡** የዩክሬን የመገናኛ አገልግሎት ሰጪ ጠቋሚት የሳይበር ጥቃት ሰለባ ነበሩ+በሩሲዮ የተያዙ ግዛቶችን በከፍተኛ ሳንሱር እና ክትትል በሚደረግባቸው የሩሲያ አውታረ መረቦች ውስጥ እንዲሆኑ መከራዎች ነበሩ።

## Africa
## Regional overview in 2022

19 የበይነመረብ እገዳዎች
12 አገሮች
2021

9 የበይነመረብ እገዳዎች
7 አገሮች
2022

**ኢትዮጵያ: 1**
ትግራይ ክልል ውስጥ የቀጠለው የበይነመረብ እገዳ እስከ 2022 መጨረሻ ድረስ 787 ቀናት ደርሷል።

**ኡጋንዳ: 1**
ፌስቡክ ላይ የቀተለው እገዳ እስከ 2022 መጨረሻ ድረስ 719 ቀናት ተቋጥሯል።

ቡርኪናፋሶ: 2 ሰራሊዮን: 2 ናይጄሪያ: 1
ሶማሌላንድ:1 ዝምባቡዌ: 1

**44.5% የበይነመረብ ገደቦችን በመቃወም ጋር ተሰልፈዋል**
ሰራሊዮን: 2 ሶማሌላንድ: 1 ዝምባቡዌ: 1

**33.3% የበይነመረብ እገዳዎች የበይነመረብን መድረኮች ኢላማ ያደረጉ ናቸው**
ቡርኪናፋሶ: 1 ናይጄሪያ: 1 ኡጋንዳ: 1

የበይነመረብ እገዳን መከታተል ከጀምርንበት 2016 ጀምሮ 2022 የተመዘገበው የበይነመረብ እገዳ ዝቅተኛው ቢሆንም፤ አፍሪካ በአለም ረግሙንና እስካሁን የቀጠለውን የበይነመብ እገዳ በኢትየጵያ ትግራየ ክልል በማስተናገድ ላይ ትገኛለች። በአፍሪካ ውስጥ ከተከሰቱ ዘጠኝ የበይነመረብ እገዳዎች ውስጥ ቢያንስ አራቱ የተከሰቱት ከተመዘገበው የሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር ተያይዞ ሲሆን፤ ከዘጠኙ እገዳዎች ቢያንስ አራቱ የተፈጸሙት ከተመዘገቡ የሰብአዊ መብት ረገጣ ጎን ለጎን ነው፣ ሁሉም አገዳዎች በተቃውሞ ሰልፎች ላይ ከደረሰ የሀይል እርምጃና በቀጠሉ ግጭቶች አውድ ውስጥ የተከሰቱ ናቸው።
በታሪክ ምርጫ በአፍሪካ ውስጥ ለበይነመረብ እገዳ ቀሰቃሽ ቦሆንም በንፅፅር በ2022 አነስተኛ ምርጫ የተካሄደበት ነበር። በ2021 በኡጋንዳ ከተካሄደው ምርጫ ጋር ተያይዞ የበይነመረብት መድረኮች ያነጣጠረ እገዳ የተጣለ ሲሆን ይህ እገዳ እስከአሁንም ቀጥሏል።[1] ተጨማሪ ምርጫዎች በ2023 ስለሚኖሩ አክሰሰናው እና #KeepItOn ጥምረት ሁኔታውን በቅርበት መከታተላቸውን ይቀጥላሉ ።.[2]

## የበይነመረብ እገዳ በአመፀና ተቃውሞ ወቅት

በቡርኪናፋሶ፣ በሴራሊዮን፣ በሶማሊላንድ እና በዚምባብዌ ያሉ ባለስልጣናት ለተቃውሞ እና ለዋና ዋና የፖለቲካ ዝግጅቶች በይነመረብን በማገድ ምላሽ ሰጥተዋል።

በህዳር 2021 የኢንተርኔት አገልግሎትን የሚዘጉ ሀገራት አሳፋሪ ዝርዝር ውስጥ ከገቡ በኋላ የቡርኪናፋሶ መንግስት ለድርጊቶቹ ምንም አይነት ማብራሪያ ሳይሰጥ በጃንዋሪ 10

1 Monitor (2022). መንግስት ከትልቁ የቴክኖሎጂ ተቋም ጋር የሚደረገው ንግግር ሲቆም፣ ፌስቡክ እንደተዘጋ ቆይቷል ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.monitor.co.ug/uganda/news/national/facebook-to-remain-shut-as-govt-talks-with-tech-giant-stall-3912172/.
2 Access Now (2022). በ2023 መከታተል ያለብን ምርጫዎች እና የበይነመረብ እገዳዎች. ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ https://www.accessnow.org/2023-elections-and-internet-shutdowns-watch/.

ለነበረ የመንግስት ተቃውሞ የሞባይል ዴታን ሙሉ በሙሉ አግዶ አዲሱን አመት ጀምሯል።[3]

ምንም እንኳን ባለሥልጣናቱ አገልግሎትን በማግሥቱ ቢመልሱም፣ መንግሥት “ብሔራዊ ደኅንነት”ን በምክንያትነት በመጥቀስ ፌስቡክን ማገዱን ቀጥሏል።[4] ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በጃንዋሪ 23፣ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሪፖርቶችን ተከትሎ፣ መንግስት በድጋሚ በመላው ሀገሪቱ የሞባይል ግንኙነቶችን አቋርጧል፣[5] ከሁለት ቀናት በኋላ አገልግሎወደነበረበት ተመልሷል።[6] በሴራሊዮን በኑሮ ውድነት የተነሳ ፀረ-መንግስት ተቃውሞ በተባባሰ ጊዜ መንግስት ተቃውሞውን ለማብረድ የግድያ የበይነመረብ እገዳን ተጠቅሟል።[7] የሴራሊዮን መንግስት ለመጨረሻ ጊዜ የኢንተርኔት አገልግሎትን የዘጋበው በ2018 በምርጫ ወቅት ነበር።[8]

በተመሳሳይ፤ በአለም አቀፍ እውቅና ባለው የሶማሊያ ድንበር ውስጥ እራሷን ራስ ገዝ አስተዳደር አድርጋ ያወጀችው ሶማሊላንድ ውስጥ በነሐሴ 2022 የፕሬዚዳንታዊ ምርጫውን መራዘሙን ተከትሎ የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ ለመቀልበስ በይነመረብ ላይ እገዳ ጥላ ነበር።[9] እገዳው በዋቁዪ ጋልቢድ ክልል እንዲሁም በደቡብ እና መካከለኛው ሶማሊያ አንዳንድ ክፍሎች ላይ የደረሰ ሲሆን፤ ለ10 ሰአታት ያህልም ቆይቷል።[10] በ 2017 የሶማሊላንድ መንግስት በምርጫ ወቅት የማህበራዊ ትስስር ገፆችን አግዶ ነበር[11]

በመጨረሻም የዚምባብዌ መንግስት በተቃዋሚ ፓርቲ የዜጎች ጥምረት ለለውጥ በተጠራው የ"ቢጫ እሁድ" ሰልፍን ለማደናቀፍ በማሰብ የበይነመረብ አገልግሎትን አቋርጧል። ዜጎች ለሰልፉ በተሰበሰቡበት ወቅት የማህበራዊ ትስስር ገፆችን ለመጠቀም ተናግረው ነበር።[12] ዚምባብዌ ከዚህ ቀደም ተቃውሞዎችን ለመቀልበስ የበይነመረብ አግልግሎትን አግዳ ነበር።[13]

## የበይነመረብ እገዳ በምረጫ ወቅት

ብዙ ጊዜ ምርጫ በአፍሪካ ከተቃውሞ እና ብጥብጥ ጋር ይያያዛል፤ ለበይነመረብ መዘጋትም እንደዋኛ መንሰኤም ይወሰዳል። ቀደም ብለን እንደገለጽነው፣ በ2022 ከምርጫ ጋር የተያያዙ የበይነመረብ እገዳዎች ቁጥር ዝቅተኛው ነበር (በኡጋንዳ ውስጥ ከ2021 ጀምሮ እየተካሄደ ያለው እገዳ እንደቀጠለ ነው)። በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ በአመቱ የነበሩ ምርጫዎች ቁጥር አነሰተኛ መሆናቸው ለዝቅተኛነቱ አስተዋፅኦ አርጓል። መንግስታት በይነመረብን እንዳያግዱ የሲቪል ማህበረሰቡ ውትወታም ከፍተኛ ነበር።

ጋምቢያ በእኛ የምርጫ ክትትል ዝርዝር ውስጥ ነበረች፤[14] ሀገሪቱ ከ2016 ጀምሮ ከምርጫ ጋር የተገናኙ የበይነመረብ እገዳ ብታደርግም፤ በመጋቢት 2022 ሀገሪቱ በህግ አውጭዎች ምርጫ ወቅት ሙሉ በሙሉ የበይነመረብ አገልግሎትን ክፍት አድርጋ ቆይታለች።[15]

---

3 Desobeissance Civile. የፌስቡክ ልጥፍ፣ ጃንዋሪ 10፣ 2022። ፌብሩዋሪ 17፣2023: https://www.facebook.com/Desobeissancecivileburkina/posts/4817989371573475/.

4 Anadolu Agency (2022). ከበይነመረብ መቋረጥ በኋላ ቡርኪና ፋሶ በይነመረብን አግዳለች። ከፌበሩዋሪ 17፣2023 የተወሰደ: https://www.aa.com.tr/en/africa/burkina-faso-restricts-facebook-after-internet-outages/2480343/.

5 Faso7 (2022). Burkina Faso: La connexion Internet mobile à nouveau coupée. ከፌበሩዋሪ 17፣2023 የተወሰደ https://faso7.com/2022/01/23/burkina-faso-la-connexion-internet-mobile-a-nouveau-coupee/.

6 Access Now (2022). ቡርኪና ፋሶ የጣለችውን የበይነመረብ እገዳ ባፋጣኝ ማንሳት አለባት። ከፌበሩዋሪ 17፣2023 የተወሰደ https://www.accessnow.org/burkina-faso-internet-shutdown/.

7 Access Now (2022). #KeepItOn በሴራሊዮን: መንግስት ፖለቲካን ለመቆጣጠር የሚያደርገውን የበይነመረብ እቀባ በአፋጣኝ ሊዮቆም ይገባል። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.africafex.org/digital-rights/sierra-leone-joins-global-trend-shuts-down-internet-and-mobile-services-during-elections__trashed/.

8 African Freedom of Expression Exchange (2018). ሴራሊዮን የአለምአቀፍን ትኩረት ተቀላቅላለች: በምርጫ ወቅት የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎትንና በይነመረብን አግዳለች። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/keepiton-in-sierra-leone/.

9 Access Now (2022). #KeepItOn በሶማሊላንድ: መንግስታት ተቃውሞንና መረጃን ማግኘነትን ማፈን አይችሉም። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/keepiton-in-somaliland/.

10 *Ibid.*

11 Africa News (2017). ሶማሊላንድ የማህበራዊ ትስስር ገፆችን በምርጫ ወቅት ልታጠፋ ነው። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.africanews.com/2017/11/11/somaliland-to-shut-down-social-networks-during-election-period/.

12 Zimbabwe Independent (2022). ሳይበርስፔስ አዲስ የፖለቲካ አውደውኪያ። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.newsday.co.zw/theindependent/amp/slider/article/4091/cyberspace-the-new-zim-political-battlefield/. ተረኺቡ

13 Al Jazeera (2019). ዚምባቡዌ ተቃውሞችን ለማፈን በወሰደችው እርምጃ በይነመረብን አግዳ ነበር። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.aljazeera.com/news/2019/1/18/zimbabwe-imposes-internet-shutdown-amid-crackdown-on-protests/.

14 Access Now (2022). #KeepItOn: የ2022 ምርጫዎችና የበይነመረብ እገዳዎች እይታ። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/elections-internet-shutdowns-watch-2022/.

15 Africa News (2016). የጃሜህ ጋምቢያ በምርጫ ወቅት በይነመረብ እንዳይቋረጥ የቀረበለትን ጥያቄ ወደጎን ትቷል። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ: https://www.africanews.com/2016/12/01/gambia-s-jammeh-slams-request-to-stabilize-internet-on-election-day/.

ኬንያ በበኩሏ በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ጎረቤቶቿ መካከል ግንባር ቀደሟ በመሆን በነሀሴ 2022 በተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ለ#KeepItOn ጥምረጥ ቆራጥነቷን አሳይታለች። ይህ ከጥር 2021 አጠቃላይ ምርጫ በፊት ፌስቡክን የዘጋችው እና እስካሁን ድረስ እገዳውን ያላነሳችው ዩጋንዳን ይጨምራል።[16]

የኬንያ በይነመረብን የመዝጋት ታሪክ የሌላት ቢሆንም፣ ነገር ግን እየጨመረ በመጣው የፖለቲካ ውጥረቱ እና እየበዛ በመጣው የሀሰተኛ መረጃዎች ስርጭት ምክንያት ምርጫ ክትትል ዝርዝራችን ውስጥ ነበረች። ከምርጫውን የተያያዘ የበይነመረብ እገዳን ለመከላከል አክሰሰናው ከጥምር አጋሮቹ ጋር በመሆን ለጋዜጠኞች፣ ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና ለምርጫ ታዛቢዎች ስልጠናዎችን ነማካሄድ በ2022 አጠቃላይ ምርጫ ወቅት የኬንያ መንግስት እና የቴሌኮም ስራ አስፈፃሚዎች ላይ የማያቋርጥ ግፊት አድርገዋል።[17]

ከኬንያ ምርጫ በፊት የወቅቱ የሀገር ውስጥ ካቢኔ ፀሃፊ ፍሬድ ማቲያንጊ መንግስት ኢንተርኔትን የመዝጋት ፍላጎት እንደሌለው ጠቁመዋል።[18] ነገር ግን መንግስት የተሳሳቱ መረጃዎችን እና የጥላቻ ንግግሮችን በትኩረት ለመከላከል እንዳሰበ ግልጽ አድርጓል።[19] የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ግሎባል ዊትነስ ባደረገው ጥናት የሜታ ፌስቡክ የጥላቻ ንግግሮችን ማስታዎቂያዎችን ማፅደቁን ካረጋገጠ በኋላ[20]

ሜታ የጥላቻ ይዘቶችን ስርጭት ለመግታት እርምጃ ካልወሰደ በስተቀር የብሔራዊ ትብብር እና ውህደት ኮሚሽን (National Cohesion and Integration Commission) በኬንያ ፌስቡክን እንደሚዘጋ ዝቶ ነበር። ኤጀንሲው ለሜታ እንዲያስተካክል የሰባት ቀናት የጊዜ ገደብ ሰጥቶ ነበር።[21] በርካታ የሲቪል ማህበራት እና በርካታ መንግስታት በምርጫው ዙሪያ ሀሳብን በነፃነት መግለጽ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ስላሰሰባቸው ይህንን ዛቻ አውግዘዋል። በመጨረሻም መንግስት በይነመረብንም ሆነ የማህበራዊ ትስስር ገፆችን እንደማይዘጋ አረጋግጧል።[22]

ከምርጫ ጋር የተያያዘ የበይነመረብ እገዳ ስጋት ሆኖ የሚቀጥል በመሆኑ አክሰሰናው እና የ#KeepItOn ጥምረት በ2023 በአፍሪካ 11 ሀገራት የሚደረጉ ምርጫዎችን ይከታተላሉ። እነዚህ አገራት ከዚህ ቀደም በይነመረብን አግደው የሚያውቁ ናቸው።[23] **በምርጫ ወቀት በይነመረብ ክፍት ሆኖ እንዲቀጥል ቆራጥነት ማሳየት ለአፍሪካ ዲሞክራሲ አዲስ መእራፍ ለመክፈት ጠቃሚ እርምጃ ነው።**

## የቀጠለ የበይነመረብ መድረኮች እገዳ

በ2021 የናይጄሪያ[24] እና የኡጋንዳ መንግስታት[25] በመንግስት ባለስልጣናት ወይም የተከታዮቻቸውን ጽሁፎችን ያስወገዱ የማህበራዊ ትስስር መድረኮች ላይ የበቀል እርምጃ ወሰደዋል። የመሣሪያ ስርዓቶች የአገልግሎት ውሉን ማሟላት ባለመቻላቸው እነዚህን ልጥፎች ካስወገዱ በኋላ፣ የመንግስት ባለስልጣናት መድረኮቹን ሙሉ በሙሉ አግደዋል። ኢንዚህ የማህበራዊ ትስስር ገፆች የመድረኩን መተዳደሪያ ደንብ ያለከበሩ ፅሑፎቹን ከገፃቸው ላይ ካስወገዱ በኋላ መንግስታቱ የማህበራዊ ትስስር ገፁን ሙሉ ለሙሉ አግደዋል።

16 The New York Times (2021). ኡጋንዳ ከአከራካሪው ምርጫ በፊት ፌስቡክን አግዳለች። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.nytimes.com/2021/01/13/world/africa/uganda-facebook-ban-elections.html/.

17 Access Now (2022). አይኖች በኬንያ ላይ: በምርጫ ወቅት የበይነመረብ ግንኑነት እንዳይቋረጥ መንግስት ቁርጠኝነት ሊያሳይ ይገባል። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.accessnow.org/kenya-government-internet-connectivity-elections/; Access Now (2022). ማስጠንቀቂያ፡ የበይነመረብ መድረኮችን ማገድ የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ያባብሳል። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.accessnow.org/kenya-online-platforms-social-media-blocking-internet-shutdown-election/.

18 The Star (2022). በምርጫ ወቅት በይነመረብን አናግድም።ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.the-star.co.ke/news/2022-06-09-we-wont-shut-down-internet-during-elections-matiangi/

19 The People Daily (2021). ማቲያንጊ፡ መንግስት በይነመረብን ባያግድም እያየናችሁ ነው። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.pd.co.ke/news/matiangi-state-wont-switch-off-internet-but-were-watching-you-83867/.

20 Global Witness (2022). በአሰጨናቂው የኬንያ ምርጫ ወቅት ፌስቡክ የብሄር ግጭት የሚቀሰቅስ ይዘት ያለው ማስታወቂየያ መመድረኩ ላይ አስተናግዶ ነበር። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.globalwitness.org/en/press-releases/facebook-approves-ads-calling-ethnic-violence-lead-tense-kenyan-election/.

21 The East African (2022). ኬንያ ፌስቡክ ላይ መአቀብ እንደመትጥል አስፈራርታ ነበር። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ *https://www.theeastafrican.co.ke/tea/news/east-africa/kenya-threatens-ban-on-facebook-over-hate-speech-3896380/.*

22 Joe Mucheru EGH (@mucheru). የትዊተር ልጥፍ. 1:48 AM. ጁላይ 30, 2022. ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ፡ https://twitter.com/mucheru/status/1553271302005334016/.

23 የሱፕራ ማስታወሻን ይመልከቱ2.

24 Access Now (2022). በናይጄርያ የትዊተርን መድረግ ማገድ ጥብቅ የሆኑ መሰረታዊ መብቶቸን መጣስ ነው። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.accessnow.org/nigeria-blocks-twitter-keepiton/.

25 The New York Times (2021). ኡጋንዳ ከአከራካሪው ምርጫ በፊት ፌስቡክን አግዳለች። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.nytimes.com/2021/01/13/world/africa/uganda-facebook-ban-elections.html/.

የናይጀሪያ መንግስት ለሰባት ወራት ሙሉ የትዊተር መደረሻን አግዷል፣ ይህም ሰፊ የህዝብ ቅሬታ አስነስቷል።[26] ባለስልጣናት እገዳውን ያነሱት በጥር 2022 ከኩባንያው ጋር ሰፊ ድርድር ካደረጉ በኋላ ነው።[27] የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች በዚህ የትዊተር እገዳ ህጋዊነት ላይ ክስ መሰርተው በ2022 የምዕራብ አፍሪካ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ የፍትህ ማህበረሰብ ፍርድ ቤት (ECOWAS Court) እገዳው ህገወጥ መሆኑን በማወጅ ጠቃሚ ድል አስመዝግበዋል።[28]

የኡጋንዳ መንግስት በበኩሉ ፌስቡክን ከሁለት አመት በላይ በመዝጋት የቀጠለ ሲሆን እስከ የካቲት 2023 ኡጋንዳውያን በቪፒኤን ብቻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።[29]

## // Ethiopia

የኢትዮጵያ የትግራይ ክልል የእርስ በርስ ጦርነት ከጀመረበት ህዳር 4 ቀን 2020 ጀምሮ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተዘግቷል።[30] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሀት) መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት - መንግስት በክልሉ ውስጥ ያሉ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ወደነበረበት ለመመለስ የገባውን ቃል በህዳር 2022 መተግበር የጀመረ ቢሆንም፤[31] የተገደበ የስልክና የበይነመረብ ግንኙነት ማየት የጀመርነው ኢትዮ ቴሌኮም የመሰረተ ልማት ጥገና ከጀመረበት ከታህሳስ 2022 ጀምሮ ነው። እስከ ፌብሩዋሪ 2023 ድረስ አብዛኛው የክልሉ ህዝብ ግንኙነቱ እንደተቋረጠ የቆየ ሲሆን፤ የበይነመረብ አገልግሎት ያገኙትም ቢሆን ከዘገየ ፍጥነት እና ከተገደበ የ2ጂ አገልግሎቶች ጋር እየታገሉ ይገኛሉ።[32]

ለአመታት በትግራይ ክልል እና በአጎራባች መህበረሰቦች ላይ የዘለቀው የበይነመረብ አገልግሎት መቋረጥ ድርጊቱ ምን ያህል አስከፊ እና አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ቁልጭ አድርጎ

**የበይነመረብ እገዳ ተፅእና ምስክርነት: ትግራይ ክልል በሰሜን አሜሪካ የምትኖር ወጣት የትግራይ ሴት**

**“ከቤተሰቤ አባላት አንዱ ስልክ ማንሳት እንደሚችል ተስፋ በማድረግ ከእንቅልፌ ስነቃ በየቀኑ የተለያዩ ቁጥሮች ለመደወል የሞከርኩባቸውን ቀናት አስታውሳለሁ። የቤተሰብዋ አባላት በህይወት እንዳሉ ወይም እንደሌሉ ሳያውቁ መቆየት የሰው ልጅ ሊደርስበት ከሚችለው እጅግ የከፋ ሁኔታ ነው። በሰው አልባ ጀቶች በሰላማዊ ሰዎች ላይ የደረሰውን ጥቃት መስማቴ አእምሮዬን እንድሰት አድርጎኛል። በትምህርት ቤቴ እና በስራዬ ላይ ማተኮር አልቻልኩም። ወንድሞቼንና እህቶቼን በህልሜ አያቸው ነበር እና ከእነሱ ጋር ለመነጋገር በጉጉት ስተብቅ ቆይቻለሁ፤ ነገር ግን ለ 2+ ዓመታት ያህል አልቻልኩም። አሁንም ቢሆን በትግራይ ክልል ሁሉም ከተሞች የኢንተርኔት አገልግሎት ሰላልተመለሰ ጥቂት የቤተሰብ አባላትን ማግኘት አልቻልኩም።”**

በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሰድስት ሚሊዮን ህዝቦች ከሌላው አለም እንዲቆራረጡ ካደረሰው ተጽእኖ ባሻገር፣ የቀጠለው የኮሚኒኬሽን ግንኙነት መቋረጥ በትግራይ ተወላጆች መሰረታዊ መብቶች ላይ ዘርፈ ብዙ አደጋችን አስከትሏል።[33] በግጭት ወቅት ከተከሰቱት ረጅም የበይነመረብ አገልግሎት እገዳዎች አንዱ በመሆኑ፣ በሰዎች ህይወት ላይም ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳርፏል።[34] አክሰስ ናው እና የ#KeepItOn ጥምረት በአገር ውስጥ ካሉ የበይነመረብ አገልግሎት እቀባው ተፋላሚ ወገኖች ስልታዊ እና ሰፊ ግድያ፣ አስገድዶ መድፈር እና ተጋላጭ በሆኑ

26 The New York Times (2022). ናይጄርያ ለ 7ወራት የጣለቺውን የትዊተር እቀባ አነሳች። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ: https://www.nytimes.com/2022/01/13/world/africa/nigeria-lifts-twitter-ban.html/

27 Access Now (2022). በናይጄርያ የትዊተርን መድረግ ማገድ ጥብቅ የሆኑ መሰረታዊ መብቶቸን መጣስ ነው። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/nigeria-blocks-twitter-keepiton/.

28 Access Now (2022). የECOWAS ፍርድቤት ድል: በናይጄርያ የትቂተር እቀባ ህገወጥ ነው ተባለ።ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/ecowas-court-nigeria-unlawful-twitter-ban/.

29 Monitor (2022). መንግስት ከትልቁ የቴክኖሎጂ ተቋም ጋር የሚደረገው ንግግር ሲቆም፤ ፌስቡክ እንደተዘጋ ቆይቷል ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ: https://www.monitor.co.ug/uganda/news/national/facebook-to-remain-shut-as-govt-talks-with-tech-giant-stall-3912172/.

30 Access Now (2023). ለአመታት በጨለማ ውስጥ የቆየችው ትግራይ ቀስ በቀስ ወደ ኦንላይን መድረክ እየተመለሰች ነው። ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/tigray-shutdown-slowly-coming-back-online/

31 United Nations News (2022). ኢትዮጵያ: በመንግስት እና በትግራይ የተደረሰው የደላም ስምምነት ‘ወሳኝ የመጀመርያ እምጃ’ ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://news.un.org/en/story/2022/11/1130137/..

32 ሱፕራ ማስታወሻን ይመልከቱ 30.

33 Access Now (2022). መታፈን፣ መታገድ በህመም ውስጥ: 15 ታሪኮች ከትግራይ የበይነመረብ እገታከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ: ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ: https://www.accessnow.org/15-stories-from-tigrays-internet-siege/..

34 Tghat (2022). የትግራይ የበይነመረብ እገዳ ተፅእኖ። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ: https://www.tghat.com/2022/02/24/impact-of-the-internet-shutdown-in-tigray/.

የማህብበረሰብ ክፍል አባላት ላይ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶችን ጨምሮ አሰቃቂ ወንጀሎችን እንዲፈጽሙ ሽፋን ሰጥቷል።[35] ከዚህም በተጨማሪ በረሃብና በተለያዩ ችግሮች ለሚሰቃዩ ማህበረሰቦች ሰብአዊ እርዳታ እንዳይደርስ አድርጓል። ሰዎች እንደ ጤና አጠባበቅ፤ የባንክ፣ የሥራ እና የትምህርት ባሉ መሠረታዊ አገልግሎቶች ላይ መተማመን እንዳይችሉ አድርጓል።

የእርስ በርስ ግጭት እና የትግራይ በትግራይ ክልል የተጣለው የበይነመረብ እገዳ አስከፊ ቢሆንም የዲጂታል መብት ተሟጋቾች እና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በማህበረሰባቸው ውስጥ እየደረሰ ያለውን የመብት ጥሰት የአለምን ትኩረት እንዲስብ ከፍተኛ ጥረት አሳይተዋል።[36] አክሰስ ናው እና የ#KeepItOn ጥምረት በአገር ውስጥ ካሉ አጋሮች እና የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ጋር በመሆን የትግራይ ተወላጆችን ድምጽ በማጉላት እና በበይነመረብ እቀባው ምበጅንያት ተጠያቂነትን እንዲሰፍን ጠይቀዋል። ከ100 በላይ የሲቪል ማህበራት እና ከ102 ሀገራት የተውጣጡ ግለሰቦችን ሰብሰበን የአፍሪካ ህብረት የበይነመረብ እቀባውን በመቃወም እርምጃ እንዲወሰድ ጠይቀዋል።[37] ኢትዮጵያ በህዳር 2022 አመታዊውን የኢንተርኔት አስተዳደር ፎረም ስታስተናግድ፣ ጥምረታችን የትግራይን ሁኔታ ዋነኛ አለም አቀፋዊ አጀንዳ ለማድረግ ሰርቷል።[38]

** በአልጄሪያ፣ ቱኒዚያ፣ ሊቢያ እና ሱዳን የበይነመረብ እቀባ ላይ መረጃ ለማግኘት የመካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ (MENA) ምዕራፍ ይመልከቱ

35 Global Voices (2021). በዛት ያለው በትግራይ በሴቶችን የሚፈፀም አሰገድዶ መድፈር በኢትዮጵያ ጦርነት መሳሪያ ሆናል። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ፡ https://globalvoices.org/2021/07/05/vicious-mass-rape-of-women-has-become-a-weapon-against-the-tigray-in-ethiopian-war/.

36 Tghat (2022). ግልጥ ደብዳቤ ለበይነመረብ አስተዳደር ፎረም ከፌብሩዋሪ 17፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.tghat.com/2022/09/11/open-letter-to-the-internet-governance-forum/.

37 Access Now (2022). ፊርማ ማሰባሰብ። ትግራይን ከበይነመረብ ጋር ለማገናኘት የአፍሪካ ህብረት አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ፡ https://www.accessnow.org/petition-au-reconnect-tigray/.

38 Internet Governance Forum (2022). የበይነመረብ አስተዳደር ፎረም አስራ ሰባት ስብሰባዎች ከፌብሩዋሪ 22፤ 2023 የተወሰደ: https://mail.intgovforum.org/IGF2022_summaryreport_final.pdf/.

**የኋላ ሽፋን**

የ#KeepItOn ዘመቻ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችንና የበይነመረብ እገዳን ለማስቆም የሚደረጉ ጥረቶችን አንድ ያደርጋል እና ያደራጃል። ዘመቻው በ2016 በሲሊኮን ቫሊ በተደረገው ራይትኮን ላይ ከ70 የሚጠጉ ድርጅቶች ጥምረት በይፋ የተጀመረ ነው። ከሲቪል ማህበረሰብ፣ ከመብት እና ከጥብቅና ቡድኖች ጀምሮ እስከ የምርምር ማዕከላት፣ ዲቴክሽን መረቦች፣ ፋውንዴሽን እና የሚዲያ ድርጅቶች ድረስ የጥምረቱ አባልነት ከ105 የአለም ሀገራት የተውጣጡ ወደ 300 በላይ አባላት ሽብሸብ በፍጥነት አድጓል።

ይህ ሪፖርት አክሰስ ናው ለ#KeepItOn ጥምረት ሳትመት ሲሆን የተፃፈው በዛክ ሮሰን፣ ፌሊሺያ አንቶኒዮ እና ካሮሊን ታኬት ከአክሰስ ናው ቡድን ጋር በመተባበር ነው።

የዚህ ሪፖርት ፀሀፊዎች ለበረከቱት አስተዋፅኦ የሚከተሉትን አካላት ማመስገን ይፈልጋሉ:- ሳጌ ቼንግ፣ ዶና ዌንትዎርዝ፣ ማርዋ ፋታፍታ፣ ራማን ጂት ሲንግ ቼማ፣ ዋይ ፍዮ ሚይንት፣ ጎልዳ ቤንጃሚን፣ አናስታሲያ ዚርሞንት ፣ ናታሊያ ክራፒቫ ፣ አንጄላ አላርኮን ፣ ብሪጅት አንድሬ ፣ ጂ ዮን ኪም ፣ ጃሚ ኮኮንያ ፣ ናምራታ ማህሽዋሪ ፣ ፒተር ሚኬ ፣ ካሴም ሞኔጃ ፣ ላውራ ኦብራይን ፣ ጋስፓር ፒሳኑ ፣ አግኒሪስ ሳሞፒየሪ ፣ ዴቪ ሲቫፕራካሳም ፣ ቼትና ኩመር ፣ ሜጋዮዴት፣ ዲጂታል መብቶችን፤ ሚአን ቡድን፣ ክላውደፌርን፣ ኢንተርኔት አውቴጅ ዲቴክሽን እና አናሊስስን (IODA)፣ ሚያንማር ኢንተርኔት ፕሮጀክት፣ አትን፣ ኬንቲክ፣ ኦፐን ኦብዘርቫቶሪ ኔትወርክ ኢንተርፈረንስን (OONI) እንዲሁም ሌሎች የ#KeepItOn ጥምረት አባላት ዳታዎችን በመመርመር፣ ጥልቅ ሀሳቦች በማካፈል ለዚህ ሪፖርት አስተዋፅኦ በማበርከታቸው ሊያመሰግኗቸው ይወዳሉ። ማንኛውም አይነት ስህተቶች፣ የ

የዲዛይንና እና የውሂብ እይታ የተሰራው በሳጌ ቼንግ ነው

**በዳታዎቻችን ላይ አስፈላጊ ማስታወሻ**

ይህ የ#KeepItOn ሪፖርት በ2022 በአክሰስ ናው እና በ#KeepItOn ጥምረትን የተመዘገቡ የበይነመረብ እገዳ ክስተቶችን ይመለከታል። አጠቃላይ የመረጃ ቋት ለመገንባት በምንሞክርበት ጊዜ መረጃችን በቴክኒካል ልኬት እና በአውድ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው፣ ለምሳሌ የዜና ዘገባዎች ወይም የግልለሰቦችን ቃል ያካትታል። ሪፖርቱን የሰራንበት ሜተዶሎጂ ጉድለት አለው ማለት ማለት ያልተዘገበ የበይነመረብ እገዳዎች ሊኖሩ ይችላሉ ይችላሉ ማለት ነው፤ ሪፖርቱ ከታተመ በኋላ አዲስ መረጃ ከተገኘ ወይም ሲገኝ ቁጥሮች ሊለወጡ ይችላሉ።
ለበለጠ መረጃ እባክዎን የሚቀጥለውን ድረገፅ ይጎብኙ
https://accessnow.org/keepiton-data-methodology

የካቲት 2023

#KeepItOn

CC BY